# ምዕራፍ ስድስት

# ጥናታዊ ጽሑፍ

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ትሰጣላችሁ፤
- ሥርዓተ ነጥቦችን፣ በተለይም ማለበሚያን (አስተሪክስን) በአግባቡ ትጠቀማላችሁ፤
- በጽሑፍ ከሚቀርቡ ሥራዎች አጠቃላይ እውነታንና የግል አስተያየትን ትለያላችሁ፤
- ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ሳይንሳዊ ግኝቶችንና የምርምር ውጤቶችን አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ጽፋችሁ ታነባላችሁ፤
- ምርምር ለማካሄድ የሚረዱ የአሠራር ቅደም ተከተሎችን ተረድታችሁ ጥናታዊ ጽሑፍ ታዘጋጃላችሁ፤
- ለጥናታዊ ጽሑፍ ሥራዎቻችሁ መጻሕፍትንና የተለያዩ ሰንጠረዦችን በማንበብ፣ እንዲሁም ቃለመጠይቅ በማቅረብ መረጃዎችን ትሰበስባላችሁ፤
- ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኛችኋቸውን ሀሳቦች በራስ አባባልና በጭምቃሳብ ትገልጻላችሁ፤
- የመረጃ ምንጮችን አጠቃቀስ ተረድታችሁ በጥናታዊ ሥራዎቻችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ።

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ሳይንሳዊ ግኝት ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ምርምር (ጥናት) ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ጠቀሜታውስ?
3. ለጥናታዊ ፅሁፍ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው ብላችሁ ትገምታላችሁ?
4. ስለምርምር ምንነትና አገልግሎት የምታውቁትን ከዘረዘራችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ከምታገኙት ሃሳብ ጋር አነፃፅሩ፡፡

## የጥናታዊ ጽሑፍ አዘገጃጀት

በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ መጥቀው አንቱ የተባሉት አገሮች ለዚህ የበቁት ለምርምር ሥራ ከፍተኛ ዋጋ በመስጠታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሀገሮች ከፍተኛ ገንዘብ፣ ብዙ ጊዜና በርካታ ለምርምር ተፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይመድባሉ፡፡ ለተመራማሪዎች ሙያዊ ነጻነት በመስጠት የተገኙትንም የምርምር ውጤቶች በሚገባ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም የእነሱን ሕይወትና አኗኗር ከመለወጥ አልፈው፣ የእኛንና የመሰሎቻችንን አኗኗር፣ ባህልና ልምድ እየተጫኑ ባንወድም በግድ እየለወጡት ይገኛሉ፡፡ ታዲያ የዚህ ሁሉ ለውጥ መንስዔው ምርምር ከሆነ፣ «ምርምር ምንድን ነው?» ብለን መጠየቃችን አይቀርም፡፡ ምርምር ሳይንሳዊ ዘዴን መሠረት አድርጎ ማኅበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ትምህርታዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ወይም በተለያዩ መስኮች አዳዲስ ትውረትን (ንድፈ ሀሳብን) ለማፍለቅ በሰዎች ወይም በሌሎች ማናቸውም ነገሮች ላይ የሚካሄድ ጥናት ነው፡፡ ምርምር ሳይንሳዊ ዘዴን መሠረት ያደርጋል ሲባል፣ ልክ እንደ ሌሎቹ የእውቀት መስኮች ህግን፣ ደንብንና ሥርዓትን ተከትሎ በተላውጦዎች (ቫሪያብልስ) መካከል የሚኖርን ግንኙነት ለመፈተሽ፣ የተከሰተን ችግር ለመፍታት ወይም የጎደለ እውቀትን ለማሟላት የሚከወን ሂደት ነው ማለት ነው፡፡

© MoE, FDRE Not to be republished

በመሆኑም ተመራማሪው ሊያከናውናቸው የሚፈልጋቸውን ተግባራት ደረጃ በደረጃ ያቅዳቸዋል፤ ይተገብራቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ሂደቱ የምርምርን ሳይንሳዊ ባህሪ የሚያሳይ ነው፡፡

አንድ ምርምር (ጥናት) ሂደት በመሆኑ ተመራማሪው ሊከተላቸው የሚገቡ ደረጃዎችና ቅደም ተከተሎች አሉ፡፡ እነዚህም ቅደም ተከተሎች ርዕስ መምረጥ፣ ስለርዕሱ በቂ ግንዘቤ መጨበጥ፣ የጥናቱን ሂደት በቅድሚያ ማቀድ፣ መረጃ ማሰባበሰብና መተንተን እና ጥናታዊ ጽሑፉን ማዘጋጀት ናቸው፡፡ ቀጥለን በአጫጭሩ እንመልከታቸው፡፡

**ርዕስ መምረጥ፡-** በጥናታዊ ጽሑፍ ዝግጅት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር የጥናታዊ ጽሑፉን ርዕስ መምረጥና መወሰን ነው፡፡ በርዕስ መረጣውም ጊዜ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች፣ ጥናቱን ለማካሄድ ያለን አቅም፣ ጊዜ፣ ገንዘብና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን በቅድሚያ መወሰን ወደፊት በሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከወዲሁ ለመፍታት ያስችላል፡፡ ርዕሱ ከተመረጠ በኋላ ይዘቱን ወስኖ (ርዕሱን አጥብቦ) በማያሻማ መንገድ በግልጽ ማስፈር ተገቢ ነው፡፡

**ስለርዕሱ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ፡-** የጥናት ርዕሱ ተመርጦና በግልጽ ተጽፎ ከቀረበ በኋላ ተከታዩ ሥራ በተመረጠው ርዕስ በቂ ግንዛቤ ማግኘት ነው፡፡ ይህም የተመረጠውን ርዕስ በሚመለከት ቀደም ሲል የተጻፉ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ መጣጥፎች፣ ጋዜጦች ወዘተ. መኖራቸውን ማረጋገጥና እነዚህንም በማንበብ በርዕሱ ላይ በቂ ሃሳብ ማግኘት ተገቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ቀደም የተሠሩ ሥራዎች በበቂ ከሌሉ፣ ጥናቱን ለማካሄድ የሚያግድ ነገር ባይኖርም፣ የሥራው ሂደት ከባድና አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አጥኚው

በቤተመጻሕፍት ብቻ ሳይወሰን፣ መረጃ ሊገኝባቸው ከሚችሉ ቦታዎች (ለምሳሌ ከቤተመዛግብት) እና ከግለሰቦች ጭምር ማሰባሰብ ይጠበቅበታል፡፡

**የጥናቱን ሂደት በቅድሚያ ማቀድ፡-** ሊካሄድ የታሰበው ጥናት ግቡን ሊመታ የሚችለው በቅድሚያ የጥናቱ አካሄድ ምን መምሰል እንዳለበት በንድፍ መልክ ተዘጋጅቶ የተቀመጠ እንደሆነ ነው፡፡ መቀመጥ ብቻ አይደለም፤ አጥኚው እየተመላለሰ የሚከተለውና እንዳስፈላጊነቱም በሂደት የሚያስተካክለው የጥናት ዕቅድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ በምን ዘዴ መካሄድ እንዳለበለትና የጥናቱ መረጃዎችም በእንዴት ዓይነት መንገድ መሰብሰብና መተንተን እንዳለባቸው የሚወሰነው በዚሁ ደረጃ ነው፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

**እዚህ ላይ ንባባችሁን ገታ አድርጉና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. እስካሁን ያነበባችሁት ቀደም ሲል ስለምርምር ካቀረባችሁት ሃሳብ ጋር ይስማማል?
2. እስካሁን ካነበባችሁትና ከምታውቁት በመነሳት የቻላችሁትን ያህል ስለጥናታዊ ጽሑፍ አዘገጃጀት በአጫጭሩ ጥቀሱ፡፡
3. ከቀሪው የምንባቡ ክፍል ምን ትጠብቃላችሁ?

**መረጃዎች መሰብሰብና መተንተን፡-** የጥናቱ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ለጥናቱ በተመረጠው/ጡት መንገድ/ዶች ነው፡፡ በመሆኑም መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ በጽሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ ወዘተ. ሊሰበሰቡ እንደሚችሉ ልብ ማለት ተገቢ ነው፡፡ ተገቢውን መረጃም ለማዘጋጀት በቅድሚያ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በጥንቃቄ ሊዘጋጁ፣ እንዳስፈላጊነቱም በባለሙያ ሊገመገሙና አስተያየት ሊሰጥባቸው



© MoE, FDRE Not to be reproduced

ይችላል፡፡ መሣሪያዎቹ በጥንቃቄ ከተዘጋጁ በኋላ መረጃዎችን ከተገቢዎቹ የመረጃ ምንጮች መሰብበሰብና በመልክ በመልኩ ማደራጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚያም በንባብ ከተገኘው ሀሳብ ጋር እያዛመዱ መረጃዎችን መተንተን ቀጣይ ሥራ ነው፡፡ በትንተና ሂደቱም እንዳስፈላጊነቱ ሠንጠረዦች፣ ምሥሎች፣ ግራፎች ወዘተ. በመጠቀም የጥናቱን ውጤት አጉልቶ ማሳየት ተገቢ ነው፡፡

**ጥናታዊ ዘገባውን ጽፎ ማዘጋጀትና ማቅረብ፡-** መረጃዎች በአግባቡ ተሰብስበው ከተነተኑ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ማጠቃለያና አስተያየት ማዘጋጀትና የጥናቱን ዘገባ የመጨረሻ መልክ አስይዞ መጻፍ ነው፡፡

የጥናቱ ዘገባ ሲዘጋጅ፣ ጽሑፉ በተለያዩ መሠረታዊ ክፍሎች ተከፋፍሎ መቅረብ አለበት፡፡ የጥናታዊ ዘገባ መሠረታዊ ክፍሎችም መግቢያ፣ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት (ወይም ክለሳ ድርሳን)፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት የሚሉት ናቸው፡፡ የጥናቱ መግቢያ የዘገባው የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን፣ ስለጥናቱ አጠቃላይ የሆነ መንደርደሪያ ሀሳብ፣ ጥናቱን ለማካሄድ ሳላነሳሱ ምክንያቶች (ወይም ችግሮች)፣ ስለጥናቱ ዓላማ ወይም ጥናቱ ስለሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ እንዲሁም የጥናቱ መካሄድ ስለሚያስገኘው ጥቅም ይገለጽበታል፡፡ ከዚህ የሚቀጥለው ደግሞ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት (ክለሳ ድርሳን) ነው፡፡ ይህ ምዕራፍ (ክፍል) በጥናቱ ርዕሰጉዳይ ላይ ቀደም ብለው የተሠሩ ሥራዎች ከተለያዩ ምንጮች ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶች፣ ከጋዜጦች፣ ከሰዎች፣ ከተቋማት ወዘተ. የሚጠናቀሩበትና የሚደራጁበት ክፍል ነው፡፡

በሦስተኛው ምዕራፍ (ክፍል) የሚቀርበው ደግሞ፣ የጥናቱ ዘዴ ተብሎ የሚታወቀውና ጥናቱ ስለሚከተለው ዘዴ፣ ስለመረጃ ምንጮች፣ ስለመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች፣ የጥናቱ ትንተና ስለሚከተለው ዘዴ (ስልት) ወዘተ. የሚገለጸው ምዕራፍ ነው፡፡ ከዘዴው ቀጥሎ የሚመጣው

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ምዕራፍ (ክፍል) የመረጃ ትንተና ነው፡፡ ይህ ክፍል በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በሥርዓቱና በአግባቡ በምዕራፍ ሦስት በተጠቀመው ዘዴ የሚተነተኑበትና የሚዳራጁበት ክፍል ነው፡፡ ከትንተናው የሚቀጥለው ክፍል የጥናቱ የመጨረሻ ምዕራፍ የሆነው የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት ነው፡፡ ይህ ክፍል ከስያሜው እንደምንረዳው ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ጥናቱ የሚጠቃለልበትና ተመራማሪው መደረግ (መሆን) ስላለበት ነገር አስተያየት የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡ ከዚያም በመጨረሻ ዋቢ ጽሑፎችን በፊደል ቅደም ተከተል አዘጋጅቶ ማያያዝ አንዱ የጥናታዊ ዘገባ የማይቀር ተግባር ነው፡፡ ከዚያ በኋላ እንዳስፈላጊነቱም የተለያዩ አባሪዎች (ካሉ) ሊያያዙ ይችላሉ፡፡

(ያለው እንዳወቀ፡፡ (1998)፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር፣* እና ከአለም እሸቱ፡፡ 1994፡፡ *መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ፡፡ ከተባሉት መጻሕፍት የተወሰደ፡፡)*

## ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፡፡**

1. የአደጉት አገሮች አሁን የደረሱበት ደረጃ ላይ የደረሱት ምን በማድረጋቸው ነው?
2. የምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ መዋላቸው የኅብረተሰብን አኗኗር ይረዳል? እንዴት?
3. ምርምር አንድ ወጥ ብያኔ አለው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?
4. ምርምር በመሠረቱ የሚካሄደው ለምንድን ነው?
5. ምርምር ሳይንስ ነው የተባለበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
6. *"ምርመር ሂደት ነው"* የተባለው ለምን ይመስላችኋል?
7. ምርምር የግል አስተያየት ነፀብራቅ መሆን የለበትም፣ ለምን?
8. የምርምር ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?
9. ለጥናት መካሄድ የግድ መኖር ያለበት ነገር ምንድን ነው?
10. አንድ የጥናታዊ ጽሑፍ መሠረታዊ ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

© MoE, FDRE
Not to be repr

፪. የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍች በቃል ተናገሩ፤ ከዚያም ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ ያሏቸውን ፍችዎች በሙሉ ጻፉና ለመምህራችሁ ኣሳዩ።

| | |
|---|---|
| 1. መጨበጥ | 6. መፍታት |
| 2. የበቁት | 7. ተላውጠዎች |
| 3. መሰብሰብ | 8. መወሰን |
| 4. መተንተን | 9. ተከሰተ |
| 5. መስክ | 10. ማደራጀት |

፫. የሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች በምንባቡ ውሰጥ ባላቸው ፍች መሠረት ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

| | |
|---|---|
| 1. መጠይቅ | 6. የሚያግድ |
| 2. ሂደት | 7. የሚከወን |
| 3. ናሙና | 8. ግንዛቤ |
| 4. መቀመጥ | 9. ማቀድ |
| 5. ምንጭ | 10. ተገቢ |

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

፩. ከሚከተሉት ጽሁፎች ውስጥ የግል አስተያየት የሆኑትንና ያልሆኑትን ሀሳቦች ለይታችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. እነዚህ ምሁራን ይህን አዲስ ዓይነት የአባትነት ባህል ሲገልጹት አባቶች ልጆቻቸውን የመንከባከብና ስሜታቸውንም ልክ እንደ እናቶች ከልጆቻቸው ጋር ማቆራኘት የጀመሩበት ነው ይሉታል። በፍሪስትንበርግ (1993) አባባል የዛሬ አባቶች የመኪና ጎማ የመቀየርን ያህል የሽንት ጨርቅንም መቀየር የሚችሉ ሥልጡኖች ናቸው።

*(ካለፈው የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የተወሰደ)*

© MoE, FDRE Not to be reproduced

2. አንዳንድ ምርምሮች (ኬቲ 1996፣ ጄፎርድስ 1989) መንከባከብ የግድ አካላዊ ተሳትፎን እንደማይፈልግ፣ አካላዊ ተሳትፎ ደግሞ የግድ ለመንከባከብ ብቻ ሳይሆን ለሌላ ዓላማም ሊውል እንደሚችል ያስረዳሉ። ሌሎች ደግሞ (ኢሺ ኩንትዝ 1993፣ ዴይ እና ሚኪ1986) ምንም እንኳ አባቶች እንደእናቶች ቤተሰብ ውስጥ በአካል ተገኝተው ልጆችን ባይንከባከቡም፣ በሀሳብና በስሜት ከቤት የማይለዩ መሆናቸውን በመገንዘብ አባቶች የራሳቸው የሆነ የመንከባከቢያ ዘዴ አላቸውና የእነሱን ባሕሪ ከእናቶች የመንከባከቢያ ዘዴ ጋር በማነፃፀር "ተንከባካቢ ናቸው" ወይም "አይደሉም" ብለን መፈረጅ "ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ ነው" ይላሉ።

*(ካለፈው የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጸሐፍ የተወሰደ)*

3. በተለያዩ ትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ ደረጃዎችና ጊዜዎች የተከናወኑት ጥናቶች የሚያስገነዝቡት፣ የንባብ ትምህርትና ልምምድ በየትምህርት ቤቶቹ የሚከናወን ቢሆንም፣ በተማሪዎቹ ላይ ግን ተፈላጊው ችሎታ ወይም ክሂል አለመታየቱን ነው። "…ተማሪዎች በደረጃቸው የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው የመገንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነና የመማሪያ ቋንቋው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብም የሚፈለገውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ብቃት እንደሌለው…" (ወንደአጥር፣ 1993 ገጽ 54) ለመገንዘብ ተችሏል።

*(ደረጀ ገብሬ፣ 2009። "የንባብ ልምድ ቅኝት በአዲስ አበባ"። Etiopian Journal of Education. Vol. XXIX No 2, pp 69-102.*

**፪. በዚሁ ክፍል በተራ ቁጥር ፩/1 የቀረበው አንቀጽ በውስጡ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አልያዘም። እናንተ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ ተጠቅማችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።**

፫. በጥናታዊ ጽሑፍ ረገድ ቀዳሚው ነገር ምርምር የሚካሄድበትን ርዕስ መምረጥ ነው፡፡ የምንመርጠውም ርዕስ ከአቅማችን ጋር የተገናዘበ መሆን አለበት፡፡

በዚህ መርህ መሠረት ከሚከተሉት አጠቃላይ ርእሰ ጉዳዮች መርጣችሁ ሁለት ሁለት ጥናት ልታካሂዱባቸው የምትችሉባቸውን የምርምር ርእሶች አዘጋጁና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ በሚሰጧችሁም አስተያየት መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

**አጠቃላይ ርዕሰ ጉዳዮች፡-**

- ወጣትነትና ኤች አይ ቪ ኤድስ
- የተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫ
- የሴትና የወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ

፬. በጥናት ሥራ ሂደት ከርዕስ መረጣው ቀጥሎ የሚመጣው ተግባር በርዕሱ ዙሪያ ከዚህ ቀደም የተሠሩ ሥራዎችን ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔት፣ ከጋዜጦች ወዘተ. በመፈለግና በማንበብ በቀጥታ ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሀሳቦች በአግባቡ መሰብሰብና ማደራጀት ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ በመረጣችሁትና ከመምህራችሁ ጋር በተስማማችሁበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ከቤተመጻሕፍት ፈልጋችሁና ዕውቀቱና ልምዱ ያላቸውን ሰዎች ጠይቃችሁ ለጥናታችሁ የሚሆን ተዛማጅ ጽሑፍ አዘጋጁና ለመምህራችሁም አቅርቡ፡፡

፭. ጥናቱን ለማካሄድ የምትከተሉትን ቅደም ተከተልና ዘዴ የተለያዩ የምርምር መጽሐፎችን በማንበብ ወይም ዕውቀቱ ያላቸውን መምህራን በመጠየቅ በቅደም ተከተል ነድፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡ በሚሰጧችሁ አስተያየት መሠረት አስተካክላችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ በማቅረብ በሚሰጡ አስተያየቶች መሠረት አስተካክሉና ጻፉ፡፡

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

፮. በጥናታዊ ጽሑፍ አዘገጃጀት ሂደት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህ መሣሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ ከምርምር መጻሕፍት በማንበብ ማስታወሻ ከያዛችሁ በኋላ፣ ለእናንተ ምርምር የሚስማማችሁ የትኛው እንደሆነ በመወሰን ለመምህራችሁ አቅርቡ፤ በሚሰጧችሁ ምክር መሠረት ከአስተካከላችሁ በኋላ መሣሪያዎቹን በጥንቃቄ አዘጋጁ፡፡

፯. በመረጣችሁት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ተገቢውን መረጃ ሰብስቡ፤ መረጃዎቻችሁንም በተገቢው መንገድ አደራጁና ለመምህራችሁ አሳዩ፤ የሚሰጧችሁን አስተያየቶች ተቀብላችሁ አስተካክሉ፡፡

፰. ከላይ ደረጃ በደረጃ የሠራችኋቸውን (ከርዕስ መረጣ እስከመረጃ መሰብሰብ ድረስ ያሉትን) ሥራዎች አንድ ላይ በሥርዓት አደራጁና አንድ ወጥ ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጁ፤ ለዝግጅቱም መነሻ ይሆናችሁ ዘንድ፣ በምዕራፉ መጨረሻ ከማጠቃለያው በፊት አንድ ናሙና ጥናት ቀርቦላችኋል፡፡ ናሙና ጥናቱ ከዋቢዎች በስተቀር ሌሎቹን የጥናት አካላት ይዟል፡፡ በዚሁ ናሙና መሠረት ጥናታችሁን ካዘጋጃችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

፱. ከሚከተሉት የማለበሚያ (የአስተሪክስ) አጠቃቀሞች ምን ተረዳለችሁ? የተረዳችሁትን ጻፉና በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻችሁና ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡ በመጨረሻም ከአንድ ማጠቃለያ ላይ ድረሱና በማስታወሻችሁ ያዙ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## ማለበሚያ (አስተሪክስ)

ሥርዓተ ነጥቦች በጽሑፍ ቋንቋ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንደላቸው ባለፉት የክፍል ደረጃዎች መማራችሁን ታስታውሳላችሁ፡፡ ዛሬ ደግሞ ማለበሚያን (አስተሪክስን) ትማራላችሁ፡፡ ማለበሚያ (አስተሪክስ) በአንድ ጥናታዊ ሥራ ውስጥ በአንድ ጉዳይ ላይ ከጥናቱ ገለጻ ውጪ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልግ ሲሆን፣ የበለጠ ማብራሪያ ለሚፈልግ አንባቢ የት ሄዶ መመልከት እንዳለበት ለመጠቆም ሲፈለግ፣ የጥቅስን መገኛ ቦታ ለማመልከት ሲፈለግ፣ አዳዲስ ወይም እንግዳ ቃላትን በበለጠ ዝርዝር ማስተዋወቅ ተገቢ ሲሆን፣ ወዘተ. ከግርጌ ማስታወሻው ጋር የምናጣቅስበት የነጥብ ዓይነት ነው፡፡ አተገባበሩም በዋናው የጥናት አካል ውስጥ በተፈላጊው ቦታ ላይ የማለበሚያ ምልክት (*) ወይም የሚጠቆመው ነገር ተከታታይነት ያለው ከሆነ ደግሞ ቁጥሮችን 1, 2 … እንጠቀማለን፡፡ እነዚህ ምልክቶች ግን፣ በግርጌ ማስታወሻውም ላይ በተመሳሳይ እንደሚጠቆሙ ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ የሚከተለው ለማለበሚያ ምሳሌ ይሆን ዘንድ የቀረበ ነው፡፡

© MoE, FDR
Not to be rep

## የንባብ ልምድ ቅኝት-በአዲስ አበባ

ደረጀ ገብሬ*

"---አብዛኞቹ አስተያየቶች መነሻቸው በቂ ጥናት ሳይሆን ነሲባዊ አስተሳሰብ፣ ግምታዊ ምደባ፣ ከፊል ምርምራዊ ማጠቃለያ ናቸው ማለት ያስኬዳል። አስተያየቶቹም የሚቀርቡት ልዩ ልዩ ልምድ፣ እውቀትና ሙያ ካላቸው ግለሰቦች ወይም እንደቡድን በሚታስቡ አካሎች ጭምር ነው።[1] በተለይ..."

(The *Ethiopian Journal of Education* No 2 December 2009. p 69 ከሚለው የተወሰደ፡፡)

(ይህ ማለበሚያው በተሠጠበት ገጽ ግርጌ ይቀመጣል)

* በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ትምህርት መምህር

[1] ደረጀ ደስታ 1986 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት 21 ቀን በ54ኛ ዓመት ቁ. 220ኛ እትሙ ዕለተ ሰንበት በገጽ 2 መጽሐፍ ያልያዘ ትውልድ በሚል ርዕስ የወቅቱን የኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ኃላፊዎችን አነጋግሮ ነበር፤

© MoE, FD
Not to be rep

## የማስታወሻ አወሳሰድና የሀሳብ መዋሻ መንገዶች

ቀጥተኛ ጥቅስ፣ ግለገለፃና ጭምቃሳብ በጥናታዊ ጽሑፍ ዝግጅት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ዋነኞቹ የሀሳብ መዋሻ መንገዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሀሳብ መዋሻ መንገዶች የየራሳቸው ባሕርያት ስላሏቸው በአጠቃቀም ረገድ የተለያዩ መንገዶችን ይከተላሉ፡፡ በመሆኑም ለአጠቃቀም ይረዳን ዘንድ እነዚህን የሀሳብ መዋሻ መንገዶች አጠር አጠር ባለ ሁኔታ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### 1. ቀጥተኛ ጥቅስ

ቀጥተኛ ጥቅስ ምንጩን በሚገባ ጠቅሰን የምንወስደው ወይም የምንዋሰው የሌላ ሰው ሀሳብ ወይም አገላለጽ ነው፡፡ ቀጥተኛ ጥቅስ በምርምር ጽሑፍ ውስጥ ሲሰፍር ከምንጩ በተገኘበት አኳኋን ቃል በቃል ይሰፍራል እንጂ በራስ አባባል ተገልጾና ተስፋፍቶ አይቀርብም፡፡ በራስ አባባል ከተገለጸ ቀጥተኛ ጥቅስ መሆኑ ይቀራልና ጥንቃቄ ይፈለጋል፡፡ ቀጥተኛ ጥቅስ በቀጥታ የተወሰደ ሀሳብ እንደመሆኑ መጠን፣ በጥናታዊ ሥራው ውስጥ ሲሰፍር እንደርዝማኔው አቀማመጡ የተለያየ ነው፡፡ አጭር ጥቅስ ሲሆን በትእምርተ ጥቅስ ተለይቶ ይቀመጣል፤ ረዥም ጥቅስ ሲሆን ደግሞ ከግራና ከቀኝ ገባ ገባ ተብሎ ይጻፋል፡፡ በዚህ ጊዜ ትእምርተጥቅስ አስፈላጊ አይደለም፡፡

**የቀጥተኛ ጥቅስ ምሳሌ፣**

ትምህርት ተኮር ጉባዔዎች ወይም ውይይቶች የሚከናወኑባቸው መድረኮች ሲዘጋጁ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የንባብ ነገር ከተነሳ ኢትዮጵያውያን የንባብ ባህላችን አልዳበረም የሚል ማጠቃለያ ሲሰጥ መስማት ልማድ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለምሳሌ ያህል አያልነህ፣ *"ግልጽና ዕውቅ በሆኑ አያሌ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ለረጂም ጊዜ ቀጭጮ ቆይቷል፡፡ ህዝቡም በማይምነት መጋረጃ ውስጥ ተሸፍኖ የቆየ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የንባብ ባሕሉ አልዳበረም" (አያልነህ 1985፣ ገጽ 2)* ሲል ይገልጻል፡፡

© MoE, FDR
Not to be rep

## 2. ግስገለፃ

በአንድ ጥናት ውስጥ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመውሰድ በግለገለፃ ማስፈር የተለመደ አሠራር ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ዘጋቢው የደራሲውን ሀሳብ ሳይለቅ በራሱ ቋንቋና በራሱ ስልት የማቅረብ መብት አለው፡፡ ግለገለፃ ከምንጩ የተወሰደውን ሀሳብ በሌላ መንገድ እንደገና የመፍጠር ያህል ነው፡፡ በግለገለፃ ሀሳብን ማስፈር ይቻል ዘንድ ከዚህ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር አስፈላጊ ነው፡፡

ሀ. አንድ ተመራማሪ ወይም አጥኚ በግለገለፃ ሊያሰፈር የሚፈልገውን የሌላ ተመራማሪ ሐሳብ በሚገባ መረዳትና የጸሐፊውንም ዓላማና ፍላጎት በትክክል መጨበጥ ይኖርበታል፤ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ትኩረት በተመላበት ሁኔታ ጥናቱን በቅድሚያ ማንበብ ተገቢ ነው፡፡

ለ. አንድን ቃል በሌላ ቃል ተክቶ ማቅረብ ወይም የቃላትን ቅደም ተከተል ማለዋወጥ ብቻውን ግለገለፃ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም በአገላለጹ ላይ ቋንቋችንና ግላዊ ስልታችን ጎልቶ መታየት አለበት፤ ማለትም ሐሳቡ እንጂ ቋንቋውና የአገላለጽ መንገዳችን የራሳችን መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ ለዚህም በተደጋጋሚ መለማመድ ወይም ሙከራ ማድረግ በጣም ይጠቅማል፡፡

ሐ. አንድ ሀሳብ በግለገለፃ ሲሰፍር የሐሳቡ ባለቤት ስምና የሕትመት ዘመኑ እንዳስፈላጊነቱም ሐሳቡ የተወሰደበት ገጽ ወይም የተወሰደባቸው ገጾች በቅንፍ ውስጥ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

**ምሳሌ፣ ከባየ ይማም (1987፡ 1) *የአማርኛ ሰዋስው የተወሰደ፣***

"ቁዋንቁዋ ሁለት የተያያዙ ዋና ዋና ተግባራት አሉት፡፡ አንደኛው፣ ሀሳብን ማስተላለፍ ሲሆን፣ ሁለተኛውና የዚሁ ነፀብራቅ የሆነው ደግሞ ማንነትን ማመልከት ወይም ማሳወቅ ነው፡፡"

**የምሳሌው ሀሳብ በግለገለፃ ሲሰፍር እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፤**

ባየ ይማም (1987) ***የአማርኛ ሰዋስው*** በተሰኘው መጽሐፉ እንደገለጸው ዋና ዋናዎቹ የቋንቋ አገልግሎቶች በሁለት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ አንደኛው አገልግሎቱ መልዕክት ከአንዱ ሰው ወደሌላ ሰው ማስተላለፊያነቱ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ፣ ከመጀመሪያው አገልግሎት የሚመነጭና የማንነት መገለጫነቱ ማለትም ስለአንድ ሰው ወይም ስለአንድ ማኅበረሰብ ማንነት ፍንጭ መስጠት የመቻሉ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት አገልግሎቶች ግን ተነጣጥለው የሚታዩ አይደለም፡፡

**3. ጭምቃሳብ**

በምርምር ሥራ ውስጥ ከተለያዩ ምንጮች ሀሳብ ለመዋስ ወይም ለማሰባሰብ አንዱ መንገድ ጭምቃሳብ ነው፡፡ ጭምቃሳብ የአንድን ጽሑፍ ፍሬ ሀሳብ በራሳችን አገላለጽ አሳጥረን የምናቀርብበት መንገድ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ግለገለፃ የሌሎችን ሀሳብ በራስ ቋንቋና አገላለጽ የምናቀርብበት መንገድ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ ጭምቃሳብ ግን የጽሑፉን ሙሉ ሀሳብ በሌላ ቋንቋና አገላለጽ የምናቀርብበት ብቻ አይደለም፡፡ ጭምቃሳብ የጽሑፉን ፍሬ ሀሳብ አሳጥረን በራሳችን ቋንቋና አገላለጽ የምናቀርብበት መንገድ ነው፡፡ ምንም እንኳ አሳጥረን በራሳችን ቋንቋ ብንጽፍም በቅንፋዊ ማስታወሻ ውስጥ የሚሰፍሩትን ነጥቦች ግን መዘንጋት አይኖርብንም፡፡ አንድን ጽሑፍ ጨምቆ የተዋጣ ጭምቃሳብ ለመጻፍ፣ ከዚህ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡

***ሀ. በጥንቃቄ ማንበብ***

ጥንቃቄ የተሞላበት ንባብ፣ ለጥሩ ጭምቃሳብ መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም የአንድን ምርምር ወይም ጥናት ዋና ሀሳብ በትክክል ለመጨበጥ እንዲቻል ደግሞ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ እንግዳ ቃልም ሲያጋጥምም፣ በመዝገበ ቃላት እየታገዙ ማንበብ የጥንቃቄው አንድ ገጽታ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ የጥናቱ ዋና ሀሳብ በትክክል ለመጨበጥ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced

### ለ. በምልክት መጠቀም

ጥናታዊ ጽሑፉ በሚነበብበት ጊዜ፣ አጫጭር ማስታወሻ ከመውሰድ ጎን ለጎን ፍሬ ፍሬ ሀሳቡን እየለዩ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ከስር በርሳስ ማስመር ወይም በሌላ አማራጭ እያመለከቱ ማለፍ (ይህ የሚደረገው ጽሁፉ የራሳችን ንብረት የሆነ እንደሆነ ነው እንጂ የጋራ መጠቀሚያ ከሆነ ግን አንድም በርሳስ ያሰመርነውን ሙልጭ አድርገን ማጥፋት፣ አለበለዚያም ደግሞ ሌላ አማራጭ መጠቀም ይገባናል) ፍሬ ሀሳቡን ለመጨበጥና ተደግሞ በሚነበብበት ጊዜ የት የት አካባቢ ላይ በይበልጥ ማተኮር እንደሚገባ ለመጠቆም ይረዳል።

### መ. ዋና ሀሳቡን ለይቶ በራስ አገላለጽ ማስፈር

በጥንቃቄ አንብበን ፍሬ ፍሬ ሀሳቡን ከለየን በኋላ፣ ተከታዩ ተግባር የጥናታዊ ጽሑፉን ማዕከላዊ ወይም ዋና ሀሳብ በራሳችን አገላለጽ ማስፈር ይሆናል።

(ከቀድሞው የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ናሙና ጥናት

**በልጅ አስተዳደግ ውስጥ አባታዊ ተሳትፎ ያለው ሚና፣**
**የኢትዮጵያ ወጣቶች እይታ**

### 1. ዳራ (መግቢያ)

በልጅ አስተዳደግ ውስጥ አባታዊ ተሳትፎ ያለውን ሚና መመርመር የተጀመረው በቅርቡ አይደለም። ይህንን በሚመለከት ከ1950ዎቹ ጀምሮ እነቦልቤ (1952)፣ ኢንጊሲሽ (1954)፣ በመቀጠልም በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ እነናሽ (1965)፣ ኮቴል ቻክ (1976)፣ ፔድርስን (1996) የመሳሰሉት ምሁራን በስፋት ያተኮሩበትና አሁን ድረስም



© MoE, FDRE Not to be republished

© MoE, FD
Not to be rep

የተመራማሪዎችን ዓይን እየሳበ የሚገኝ፣ ሰፊ የጥናት መስክ ነው፡፡ በ1950ዎቹ የተደረጉት ምርምሮች አባቶች እንደሁለተኛ ወላጆች የሚታዩና ለልጆቻቸውም ራቅ ያለ ስሜት ያላቸው መሆኑን ሲያሳዩ፣ የ1960ዎቹና የ1970ዎቹ ጥናቶች ደግሞ ያባትነት ሚና ካለፈው ለውጥ እያሳየ መምጣቱን ገልፀዋል፡፡ በዚህ ረገድ አንዳንድ አባቶች፣ ለቤተሰብ ገቢ ከማስገኘትም አልፈው፣ በቤት ውስጥ ሥራም መሳተፍ መጀመራቸውን እነዚህ ጥናቶች አመልክተዋል፡፡ ይህ ለውጥ በ1980ዎቹና በ1990ዎቹ ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ፣ ይህንን ለውጥ መነሻ አድርገው የቤተሰብ ጉዳይ ተመራማሪዎች፣ “አዲስ ዓይነት የአባትነት ባህል” እየተፈጠረ መምጣቱን ይገልፃሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ፍሬስ ትንበርግ (1988)፣ ላሮሳ (1988)፣ ኘሌክ (1983)፣ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን ይህንኑ አዲስ ዓይነት የአባትነት ባህል ሲገልፁት፣ “አባቶች ልጆቻቸውን የመንከባከብና ስሜታቸውንም ልክ እንደናቶች ከልጆቻቸው ጋር በብቃት ማቆራኘት የጀመሩበት ነው” ይሉታል፡፡ በፍሪስ ትንበርግ (1993) አባባል “የዛሬ አባቶች የመኪና ጎማ የመቀየርን ያህል የሽንት ጨርቅም መቀየር የሚችሉ ሥልጡኖች ናቸው፡፡”

ሆኖም ግን ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የተደረጉትን እነዚህን ምርምሮች ስናጤን፣ ሶስት መሠረታዊ ችግሮች እናይባቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ሁሉም ምርምሮች ትኩረት ያደረጉት የአባትነት ፀጋ በደረሳቸው ወንዶች ላይ ብቻ ነው፡፡ መሠረታዊው ግንዛቤያቸውም አባትነት የሚጀምረው፣ ግለሰቡ ወላጅ አባት ሲሆን ብቻ እንደሆነ አድርጎ ከመገመት የመነጨ ይመስላል፡፡ አባትነት ግን የሚጀምረው ወላጅ ከመሆን ረዥም ዓመታት በፊት ነው፡፡ እንዲያውም ገና ከልጅነት ጊዜያችን ጀምሮ በጨዋታ ሂደት የአባትነትን ሚና እንጫወታለን፡፡ ወላጆች ከመሆናችን በፊት ወደአባትነት የሚያስገቡንን ክህሎት፣ ልምዶች፣ ፍላጎቶችና ባህሪያት እንማራለን፡፡ በተለይ የጉርምስና ዘመናችን የወንድነትን ባህሪና ስብዕና የምንመሠርትበት ወቅት እንደመሆኑ መጠን፣ የአባትነትንም ስብእና በስፋት እናዳብራለን፡፡ ታዲያ

በዚህ የአባትነት መጀመሪያ ወቅት፣ “ባለ ተስፋ አባቶች” ማለትም ለአካለ መጠን የደረሱት ጎረምሶች ልጅ በማሳደግ ረገድ “የአባትነትን ሚናን እንዴት ይመለከቱታል?” ለሚለው ጥያቄ እስከአሁን ከተደረጉት ምርምሮች ምንም ፍንጭ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ሁለተኛም ያለፉት ምርምሮች ችግር፣ ሁሉም የተደረጉት በአደጉ አገሮች በሚገኙ አባቶች ላይ ብቻ ከመሆኑ ይመነጫል፡፡ በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች የሚገኙ አባቶች ባህርይ ምን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ የሁለቱ አገሮች አባቶች በሁለት እጅግ የተለያዩ ባህሎች ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸውና የአባትነት ባህሪያቸውም ልክ እንደየባህላቸው የሚለያይ በመሆኑ፣ ካደጉት አገሮች ልምድ ተነስተን በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ስለሚገኙ አባቶች አስተያየት መስጠቱ የተደረሰበትን መደምደሚያ ስህተት ያደርገዋል፡፡ የአደጉት አገሮች ባህል “እኔነት” የተንሰራፋበት ሲሆን፣ በማደግ ላይ የሚገኙ የአፍሪካና የእሲያ አገሮች ባህል ደግሞ “እኛነት” በስፋት የሚታይበት ነው፡፡ እኛነት መተባበርን፣ መደጋገፍን፣ መረዳዳትን፣ አብሮ መኖርን የሚያጠቃልል ስለሆነ፣ የአባትነት ሚናም በዚህኛው ባህል ሲታይ፣ “እኔነት” ከበዛበት ካደጉት አገሮች ባህል የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ “እንዴት ይለያል?” ለሚለው ጥያቄ ግን፣ አሁንም ቀደም ካሉት ምርምሮች የምናገኘው ምላሽ የለም፡፡

ሦስተኛውና ዋነኛው ችግር፣ “የአባትነትን ተሳትፎ” ከመተርጎምና ከመረዳት ጋር ተያይዞ የመነጨ ይመስላል፡፡ ካለፉት ምርምሮች የምንረዳው “የአባትነት ተሳትፎ” አንድ ገፅታ ብቻ ያለው መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ነው የጥንቶቹ ምርምሮች፣ አባቶችን “በልጅ አስተዳደግ ረገድ ተሳትፎ የማያደርጉ፣ በርቀት የሚገኙ” ብለው ሲኮንኑ፣ የአሁኖቹ ደግሞ “የለም አባቶች ተለውጠዋል፤ ልክ እንደእናቶች በቅርበት ልጆቻቸውን መንከባከብ ጀምረዋል” ብለው ሲያወድሱ የሚታዩት፡፡ ልዩነቱ መኮነንና ማወደስ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ይዘታቸው አንድ ነው፡፡ ሁሉም የሚሉት፣ መንከባከብ ማለት በአካል ለልጆች ቅርብ ሆኖ ፍላጎታቸውን ማሟላት፣ ችግራቸውን ማድመጥና እርዳታ ማድረግ

© MoE, FD
Not to be rep

ነው፡፡ ይህ ምናልባት አግባብነት ያለው እንክብካቤ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ግን አባቶች የተለየ የመንከባከብ ትርጉም ቢኖራቸውስ? ወይም ደግሞ ሕፃናትን መንከባከብ ከዚህ በተለየ መንገድ ሊገለፅ ይገባዋል ብለው የሚያምኑ ቢሆንስ? እንዲያውም በአካል ከልጆቻቸው ጋር በቅርበት መገኘት ህፃናትን “አጉል” ነገር ማስተማር ስለሆነ፣ ከልጆች ራቅ ብሎ ልጆች “ራስን መቻል”፣ “ጥንካሬን” “በራስ መተማመንን”፣ ወዘተ. እንዲያውቁ መርዳት፣ “ሳይንከባከቡ መንከባከብ” አይደለምን ብለው ቢያምኑስ? ለምሳሌ በአንድ ወቅት አንድ አባት “ለምንድን ነው ልጅህን አቅፈህ ስትስመው የማትታየው” ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ፣ “ልጄ እንዲለምደኝ አልፈልግም፤ ሲያጣኝ እንዲሳቀቅብኝ ስለማልፈልግ” በማለት የእሱ አባት በሞተ ጊዜ እሱ ምን ያህል ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ተሰምቶት እንደነበር ተናግሯል፡፡

በተጨማሪም አንዳንድ ምርምሮች (ኬቲ 1996፣ ጆሮርድስ 1989) መንከባከብ የግድ አካላዊ ተሳትፎን እንደማይፈልግ፣ አካላዊ ተሳትፎ ደግሞ የግድ ለመንከባከብ ብቻ ሳይሆን፣ ለሌላ ዓላማም ሲውል እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ (ኢሺ ኩንትዝ 1993፣ ዴይ እና ሚኪ 1986) ምንም እንኳን አባቶች እንደእናቶች ቤተሰብ ውስጥ በአካል ተገኝተው ልጆችን ባይንከባከቡም፣ በሀሳብና በስሜት ከቤት የማይለዩ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ አባቶች የራሳቸው የሆነ የመንከባከቢያ ዘዴ አላቸውና የእነሱን ባህሪ ከእናቶች የመንከባከቢያ ዘዴ ጋር በማነፃፀር፣ “ተንከባካቢ ናቸው” ወይም “አይደሉም” ብለን መፈረጅ “ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ” ነው ይላሉ፡፡

እንግዲህ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ነጥቦች መነሻ በማድረግ ነው፣ ለአባትነት እየተዘጋጁ ያሉትንና በማደግ ላይ ባለ አገር ባህል ውስጥ የሚገኙት የኢትዮጵያ ወጣቶች “አባትነት ምንድን ነው ይላሉ? አባትነትንስ እንዴት ይገልፁታል? የሚሉትን ጉዳዮች ለማጥናት የተነሳነው፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## 2. የጥናቱ አላማ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች በማንሳት የኢትዮጵያን ወጣቶች የአባትነት ግንዛቤ ይመረምራል፡፡

1ኛ. "የአባቶችን የልጅ አስተዳደግ ተሳትፎ" በተመለከተ የኢትዮጵያ ወጣቶች ግንዛቤ ቀጥተኛ እንክብካቤ የማድረግን ሚና ብቻ ያሳያል? ወይስ ቀጥተኛ ያልሆነ እንክብካቤ መኖሩንም ይጠቁማል?

2ኛ. የኢትዮጵያ ወጣቶች፣ ያባቶችንስ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? ልጆችን ለመንከባከብ ብቻ ነው ይላሉ? ወይስ ቀጥተኛ ተሳትፏቸው ልጆችን ከመንከባከብ ባሻገር ለወንድነት ተግባር ማስፈፀሚያ ሊሆንም ይችላል ይላሉ?

3ኛ. በተሳትፎ ወቅት የአባቶችን ሚና እንዴት ይመለከቱታል? አባቶች ከአድራጊነት ይልቅ ልጆች ድርጊቶችን እንዲያደርጉ ምን የመገንባት ሚና ነው የሚጫወቱት ይላሉ?

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት አላማ፣ አባትነት በኢትዮጵያ ምን ይመስላል? በተለይ የኢትዮጵያ ወጣቶች በዚህ ረገድ ያላቸው ግንዛቤ ምንድን ነው? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ መረጃ አሰባስቦ በመፈተሽ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

## 3. የጥናቱ ዘዴ

### 3.1. ናሙና

554 ያላገቡ ጎረምሳ (እድሜያቸው ከ14 እስከ 19 የሆኑና ዕድሜያቸው በአማካይ 16 የሆነ) ተማሪዎች (ከ9ኛ እስከ 12ኛ ያሉ) በአዲስ አበባ ከሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በነሲብ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠው በናሙናነት ተወስደዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 55% ያህሉ ወንዶች ሲሆኑ፣ የተቀሩት 45% ያህሉ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

© MoE, FDR
Not to be rep

### 3.2 የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያ

መረጃ ለማሰባሰብ የጽሑፍ መጠይቅ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ መጠይቁም አራት ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡ ክፍል አንድ፣ የልጅ እንክብካቤ ተግባራትን ይዘረዝራል፡፡ ክፍል ሁለት ደግሞ ልጅን ራስ የማስቻል ተግባራትን ይዘረዝራል፡፡ ክፍል ሦስት፣ ልጅን ስለወንድ ፆታ የማስተማርን እንቅስቃሴዎች ይዘረዝራል፡፡ ክፍል አራት ደግሞ ሥነሥርዓትን ለማስተማር ስለሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና እርምጃዎች ይዘረዝራል፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ አምስት አምስት ተግባራት ሲዘረዘሩ፣ በአጠቃላይ የአባትን ተሳትፎ ያመለክታሉ የተባሉ 20 ተግባራት ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ መላሾችም እያንዳንዱን ተግባር ካነበቡ በኋላ፣

1ኛ. አባቶች ምን ያህል ተግባሩን (ልጆች መንከባከቡን) ራሳቸው ያከናውናሉ? ለሚሉት ከ1 እስከ 5 በሚደርሱ ነጥቦች ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ (1 ዝቅተኛውን ሲያመለክት፣ 5 ከፍተኛውን ያመለ ክታል፡፡)

2ኛ. አባቶች ምን ያህል ራሳቸው ተግባሩን (ልጆች መንከባከቡን) ከማከናወን ይልቅ እናቶች እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ? ለሚሉ ትም እንዲሁ ከ1 እስከ 5 ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ (1 ዝቅተኛውን ሲያመለክት፣ 5 ከፍተኛውን ያመለክታል፡፡)

በዚህ መልክ የተገኘው ምላሽ ተሰባስቦ እየተጠናቀረ እንዲተነተን ተደርጓል፡፡

### 3. የጥናቱ ግኝት

ከፍ ሲል ተግባራዊ በተደረጉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት መረጃዎች ተሰብስበው ሲተነተኑም የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሰረት አንኳር የሆኑትን የዚህን ጥናት ግኝቶች ብቻ ከዚህ በታች እንመልከት፡፡

© MoE, FDR
Not to be rep

1ኛ. በናሙናነት የተወሰዱት የኢትዮጵያ ወጣቶች የሰጡት ምላሽ እንደሚያሳየው የአባትነት ተሳትፎ፣

- ቀጥተኛ ብቻ ሳይሆን ተዘዋዋሪ መልክም አለው፤ ማለትም፣ ልጆችን እንደእናቶች በቀጥታ መንከባከብ ሳይሆን፣ በተዘዋዋሪ ራቅ ብሎ የመንከባከብ ሁኔታ እንደሚያሳዩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡
- በአድራጊነት ብቻ ሳይሆን፣ ልጆችም ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ ከማስቻልም አኳያ ሊታይ ይችላል፡፡ ይህም ለልጆች የሚፈልጉትን በቀጥታ በማድረግ ላይ የሚመሰረት ሳይሆን፣ ልጆች ድርጊቶችን በራሳቸው ማከናወን ይችሉ ዘንድ አቅም በመገንባት ላይ የሚያነጣጥር ነው፡፡
- ለመንከባከብ ብቻ ሳይሆን፣ ለወንድነት ፍላጎት ማስፈፀሚያ የሚውል ነው፡፡ በዚህም መሠረት መረጃዎቹ ባሕሉ ለወንድ ከሚሰጠው ቦታ የመነጨ፣ መቆጣጠርን፣ ማዘዝንና የመሳሰሉትን የወንድነት ባህሪያት ለማስተማር ሊውል እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

2ኛ. ከላይ በተጠቀሱት የአባቶች ተሳትፎዎች መካከል ከፍተኛ ግንኙነት አለ፡፡ ከፍተኛ የሆነ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚያደርጉ፣ ከፍተኛ የሆነ ተዘዋዋሪ ተሳትፎም አላቸው፡፡ በአድራጊነት ሚና የሚሰማሩ አባቶች፣ ልጆች አድራጊዎች እንዲሆኑም ያደርጋሉ፤ ለመንከባከብ የሚሳተፉት ለወንድነት ፍላጎት ተግባርም ይሰተፋሉ፡፡

3ኛ. ምንም እንኳን ከላይ በተጠቀሱት ሶስት ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ግንኙነት ቢኖርም፣ በመካከላቸው ከፍተኛ የሆነ ልዩነትም ታይቷል፡፡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማለት ተዘዋዋሪ ተሳትፎ ማለት አይደለም፤ በአድራጊነት መሳተፍ ማለት ልጆች እንዲያደርጉ መርዳት ማለት አይደለም፤ ልጆችን ለመንከባከብ መሳተፍ ማለት ለወንድነት ፍላጎት ሲባል መሳተፍ ማለት አይደለም፡፡

## 4. ማጠቃለያ

ከጥናቱ ግኝት መረዳት የሚቻለው፣ እንደኢትዮጵያ ባሉና በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ያሉ ወጣቶች ለአባትነት ያላቸው እይታ ብዙ ገፅታ

© MoE, FD
Not to be rep

ያለው መሆኑን፣ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ማለት ልክ እናቶች እንደሚንከባከቡት ዓይነት መንከባከብ ብቻ ሳይሆን፣ ለወንድነት ፍላጎት ማስፈፀሚያ ሊሆን የሚችል መሆኑንና (ለምሳሌ መቆጣጠር፣ ማዘዝ፣ የወንድነት ባህሪን ማስተማር ወዘተ.) ቀጥተኛ ተሳትፎ ያለማድረግ ማለት ያለመንከባከብ ያለመሆኑን ነው፡፡ ይህ በተለይ እንክብካቤን አስመልክቶ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ በርቀት ሆኖ የልጆችን ሁኔታ መከታተል መንከባከብ ነው ብለው አባቶች ሊያምኑ የሚችሉ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ምናልባት በአካል ከልጅ ጋር የማይታየው ግለሰብ ልጁን አይንከባከብም ቢባልም፣ እሱ ግን የሚያውቀው ያለመንከባከቡን ሳይሆን፣ ይልቁንም የበለጠ እየተንከባከበ መሆኑን ነው፡፡ በእርግጥ ይህን ዓይነት አመለካከት አባቶች ልጆቻቸውን በመቅረብ ማሳለፍ የሚያስፈልጋቸውን ጊዜና ማጥፋት ያለባቸውን ጉልበት ላለማጥፋት የፈጠሩት የብልጣብልጥነት ዘዴ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ ወይም ወደልጆች መቅረቡ "የሴትነትን ሥራ" ማከናወን መስሎም ስለሚታያቸው፣ ከዚህ ለመሸሽ ሳያውቁት የፈጠሩት የመከላከያ ዘዴ ልንለውም እንችላለን፡፡ ምናልባትም አባቶች የበለጠ እንዳይቀየሩና ሴቶች ወደአደባባይ በወጡ ቁጥር እነሱም በተራቸው ወደቤት ውስጥ ዘልቆ የመግባትን የባህርይ ለውጥ እንዳያመጡ ያደረገው ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ለማንኛውም ወንዶችን መረዳት ካስፈለገ አሁን ካላቸው አተያይ ጋር (ያላቸው አተያይ የተሳሳተም ሊሆን ይችላል) ልንረዳቸው ይገባል፡፡ የለውጥ መጀመሪያው ችግርን ማወቁ ነውና፡፡

(ምንጭ፡- በላይ ተፈራ፣ 1993፡፡ "በልጅ አስተዳደግ አባታዊ ተሳትፎ፣የኢትዮጵያ ወጣቶች እይታ፡፡" ያልታተመ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡፡)

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

፩. በኢትዮጵያ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ከሚተላለፉ የምርምር ውጤት ዘገባዎች (ለምሳሌ በሳይንስ፣ በጤና፣ በትምህርት ...) አንዱን መርጣችሁ አዳምጡና የጥናቶቹን ውጤቶች በአጭሩ በማስታወሻችሁ ጻፉ፤ ከዚያም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

፪. በምርምር ዘገባዎቹ መሠረት ለምርምሮቹ መካሄድ ሰበብ የሆኑት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ፣ ምርምሮቹ የተካሄዱባቸው አጠቃላይ ደረጃዎች ምን እንደሚመስሉ ማስታወሻ ከያዛችሁ በኋላ ከላይ ካነበባችሁት የምርምርን አዘገጃጀት የሚመለከት ምንባብ ጽንሰ ሀሳብ ጋር በማስተያየት ያሳችሁን አስተያየት በአጭሩ ተናገሩ::

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለምርምር የቀረበላችሁን ምንባብ አንብባችሁ የተረዳችሁትን ሀሳብ በቃልና በጽሑፍ ገልጻችኋል፡፡ በጽሑፋችሁም ውስጥ ሥርዓተ ነጥቦችን በተለይም ማለበሚያን (አስተሪክስን) በአግባቡ ተጠቅማችኋል፡፡ ከዚያም በጽሑፍ ከሚቀርቡ ሥራዎች ውስጥ ዕውነታንና የግል አስተያትን መለየትን በተግባር አሳይታችኋል፡፡ መዝገበ ቃላትንና ዓውድንም በመጠቀም የቃላትን ፍቺዎች መስጠትና በዓረፍተነገርም ውስጥ መጠቀም ችላችኋል፡፡ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የተላለፉ ሳይንሳዊ ግኝቶችንና የምርምር ውጤቶችን አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ይዛችኋል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ምርምር ለመሥራት የሚረዱ የአሠራር ቅደም ተከተሎችን፣ ለጥናታዊ ጽሑፍ ሥራዎቻችሁ ከመጻሕፍት፣ ከተለያዩ ሰንጠረዦችና ከቃለ መጠይቆች የመረጃዎችን አሰባሰብ፣ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኛችኋቸውን ሀሳቦች በግለገለጻና በጭምቃሳብ መግለጽን፣ የመረጃ ምንጮችን አጠቃቀስ በመረዳት በጥናታዊ ሥራዎቻችሁ ውስጥ መጠቀምን በተግባር ተለማምዳችኋል፤ በደረጃችሁም አንድ ወጥ ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅታችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ጥናታዊ ጽሑፍ ከሌላው ጽሑፍ በምን ይለያል?
2. ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሠራ ምን ምን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው?
3. የጥናታዊ ጽሑፍ ዋና ዋና ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

© MoE, FDR
Not to be repr

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አንብቤ የተረዳሁትን ሀሳብ በቃልና በጽሑፍ መግለጽ ችያለሁ:: | | | |
| 2 | ሥርዓተ ነጥቦችን በተለይም ማለበሚያን በአግባቡ መጠቀም ችያለሁ:: በጽሑፍ ከሚቀርቡ ሥራዎች ውስጥ ዕውነታንና የግል አስተያየትን መለየት እችላለሁ:: | | | |
| 3 | መዝገበ ቃላትን በመጠቀም የቃላትን ቀጥተኛ ፍች መስጠት ችያለሁ፤ | | | |
| 4 | ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ሳይንሳዊ ግኝቶችና የምርምር ውጤቶች አዳምጬ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ እችላለሁ:: | | | |
| 5 | የጥናታዊ ጽሑፍ ቅደም ተከተሎችን ተረድቼ ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጃለሁ:: | | | |
| 6 | ከመጻሕፍት፣ ከተለያዩ ሰንጠረዦች፣ ከቃለመጠይቆች ወዘተ. መረጃ መሰብሰብ እችላለሁ፤ | | | |
| 7 | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኟቸውን መረጃዎች በግለገለጻና በጭምቃሳብ መግለጽ እችላለሁ:: | | | |
| 8 | በአጠቃላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ማዘጋጀት ችያለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምእራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::